በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የፋይናንስ ቢሮ

የአምስት ዓመት /2014-2018/

የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ግንቦት 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 3

1.1. አጠቃልሎ/Executive Summary/ 3

1.2. መግቢያ 4

1.3. የሪፖርቱ ዓላማ 4

1.4. የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች 5

ክፍል ሁለት 6

2. **የዋና ዋና (አበይት) ግቦች አፈጻጸም** 6

ክፍል ሶስት 45

3. **የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እና የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች** ----------
45

3.1. ጠንካራ ጎን 45

3.2. የነበሩ ድክመቶች 45

3.3. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች 46

3.4. የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃዎች 46

3.5. በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 47

ማጠቃለያ 48

የፋይናንስ ቢሮ ከ2014 እስከ 2017 በጀት ዓመት /የ4 ዓመት/ **እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ንፅፀር** 49

ክፍል አንድ

1.1. አጠቃላይ/Executive Summary/

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የከተማውን ራዕይ እውን ከማድረግ አንጻር በአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 84/2016 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በ2023 የከተማዋን ሀብት በብቃት በማስተዳደር ፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ ልማት በማረጋገጥ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ከተሞች አንዱ ሆና ማየት የሚለውን ራዕይ በመያዝ እና ለከተማው ነዋሪ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን በጀት በመደልደል፣ በመከታተል፣ በመደገፍ እንዲሁም ጠንካራ የአሰራር ስርዓት በመርጋት አፈጻጸሙን በመከታተል የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ በማድረግ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል።

በመሆኑም ቢሮው የ10 ዓመት የፍኖተ ብልጽግና እና የ5 ዓመቱን /2014-2018/ ስትራቴጂክ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ለተገልጋዩ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሳደግ በየበጀት ዓመቱ ፍትሃዊ የሀብት አመዳደብ እና አጠቃቀም ውጤታማነትን በማሻሻል፣ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የተወጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በማሳደግ፣ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን በማሻሻል ረገድ የሚበረታታ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል።

በዚህም መሰረት የከተማ አስተዳዳሩን የወጪ እና የገቢ አስተዳደር ስርዓት ለማሻሻል የሚያስችል እና የልማት ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡ የተለያዩ ጥናቶች በማጥናት፣ ፍትሃዊና አሳታፊ የበጀት ድልድልና ውጤታማ አስተዳዳር በማከናወን፣ የልማት ፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ፣ የከተማ አስተዳደሩ ሂሳብ በወቅቱና በጥራት ተዘግቶ ለሚመለከተው አካል ተደራሽ በማድረግ፣ የመንግስት የልማት ክፍተት የሚሞላ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ፕሮጀክት እንዲበለጽግ እና ተግባራዊ እንዲሆን፤ የግዢ ስርዓት በውጤታማነት እና በዕቅድ እንዲመራ በማድረግ፣ የፋይናንስ አስተዳዳር ስርዓቱን ተከትሎ ባለመፈጸም የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ፣ ጠንካራ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በማጎልበት እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል።

1.2. መግቢያ

የፋይናንስ ቢሮ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት የከተማውን የልማት ፍላጎት መነሻ በማድረግ ሀብት አቅርቦት፣ የመደልደል፣የመቆጣጠር፣ የፋይናንስ አሰራር ሥርአትን የመዘርጋት ተግባራትን በማከናወን በከተማው የልማትና መልካም አስተዳዳር እንዲረጋገጥ በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን ባለፉት አራት በጀት ዓመታት /2014-2018/ ተቋሙ የተቋቋመለትን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ከ10 እና 5 ዓመት ፍኖተ ብልፅግና የልማት ዕቅድ ላይ የተመላከቱ ተግባራትን ከተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ ጋር የተሳሰረ ዕቅድ በማዘጋጀት የሴክተሩ አመራር፣ ባለሙያ እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሲከናወኑ ቆይተዋል።

ሪፖርቱ ከ2014-2018/ በጀት ዓመት ታቅደው የተከናወኑ እና፣ ዕቅዱን ውጤታማ እንዲሆን ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረመልሶችንና ምክረሀሳቦችን በመስጠት የቀጣዩን 5 ዓመታት የልማት ዕቅድ በውጤታማነት ለማሳካት ያስችል ዘንድ ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ለማድረግ ነው።

የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱ በሶስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን በክፍል አንድ አጠቃልሎ፣ መግቢያ፣ የተቋሙ ራዕይ ተልዕኮና እሴቶች እና የሪፖርቱ ዓላማ አስፈላጊነትን፣ በክፍል ሁለት በተቋሙ ታቅደው የተከናወኑ ዋና ዋና ስትራቴጂክ ግቦች ዓላማና ተግባራት አፈጻጸም፣ በክፍል ሶስት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ፣የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች እና ማጠቃለያ አካትቶ ቀርቧል።

1.3. የሪፖርቱ ዓላማ

በቢሮው ባለፉት አምስት በጀት ዓመት /2014-2018/ በዕቅድ የተያዙ ተግባራት አፈጻጸም፣ የታዩ ዋና ዋና ጥንካሬዎችን ለማስቀጠል፣ የተስተዋሉ ውስንነቶችን ለማረም እና በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አቅዶ ለመስራት እና ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ለማድረግ ነው።

1.4. የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

ራዕይ

- በ2022የከተማዋን ሃብት በብቃት በማስተዳደር ፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ ልማት በማረጋገጥ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ከተሞች ውስጥ አንዱ ሆና ማየት።

ተልዕኮ

- ለከተማው ነዋሪ ብልጽግና እንዲመጣ የፊስካል ፖሊሲ እና የገቢ ጥናት በማከናወን፣ አሳታፊና ፍትሃዊ የበጀት ድልድል በማድረግ፣ የመንግስትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸውን ተከታትሎ በመገምገም፣ ዘመናዊ ቀልጣፋና ውጤታማ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋትና የአስተዳደሩን ሀብት በአግባቡ በማስተዳደር ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲረጋገጥ ማድረግ።

የአሰራር መርሆዎች

- የህዝብ አገልጋይነት
- ታታሪነትና ውጤታማነት
- የህግ የበላይነትን ማክበር
- የአገርና የህዝብ ፍቅር

ዕሴቶች

- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ፍትሃዊነት
- ጥራት ያለው አገልግሎት
- በእውቀት መመራት
- ለለውጥ ዝግጁነት
- አሳታፊነትና በቡድን መስራት
- ለሀብት ውጤታማነትና ለልማት ስራዎች ዘላቂነት መጣር፣
- ሌብነትንና አድሎአዊነት መጸየፍ

ክፍል ሁለት

2. የዋና ዋና (አበይት) ግቦች አፈጻጸም

በተቋሙ ከ2014 - 2018 በጀት ዓመት ታቅደዉ የተከናወኑ ዋና ዋና ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዓላማዎችና ዝርዝር ተግባራት (ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች/Key Performance Indicators)፣

ግብ-1. የሀብት አመዳደብ እና አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል፣

ዓላማ-1. የልማት ሀብት አቅርቦት ማሳደግ፤

በየበጀት ዓመቱ ለሁሉም ገቢ ሰብሳቢ ተቋማት በገቢ ኮድ፣ በገቢ አርዕስትና በወራት የተከፋፈለ የገቢ እቅድ በማዘጋጀት ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ በ2014 ከነበረበት ብር 69 ቢሊየን በ2018 ብር 360,07ቢሊየን ማድረስ ተችሏል።

የከተማ አስተዳዳሩን የልማት ሀብት አቅርቦትን ከማሳደግ አንጻር ለአብነት የቤት ኪራይ ገቢ ግብር እና የቤት ሽያጭ ገቢ ግብር፣ የቤት ግብር ማሻሻያ፣ የመንግስት አገልግሎት ክፍያ ማሻሻያ ደንብ ከ2014 እሰከ 2018 በጀት ዓመት ከተለያዩ ተቋማት ለሚቀርቡ የዋጋ ማሻሻያ ጥያቄዎች ጥናቶችን በማካሄድ ፀድቆ ተግበራዊ ተደርጓል።

ለአስፈጻሚ አካላት፤ ለባለድርሻ አካላት፤ ለሰራተኞች፤ እና ለሚመለከታቸው ሁሉ በቤት ግብር አተገባበር የአሰራር ስርአት ዙሪያ ስልጠና በመስጠት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፤

የተገኙ ውጤቶች

በአምስት አመቱ ከቤት ግብር በ2014 በጀት ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ይሰበሰብ የነበረው 47.5 ሚሊዮን ብር ተሻሽሎ በመተግበሩ በ2015 በጀት ዓመት ብር 1.99 ቢሊዮን፣ በ2016 በጀት ዓመት ብር 7.73 ቢሊየን፤ በ2017 በጀት ዓመት አፈጻጸሙን በማሳደግ ወደ ብር 8.46 ቢሊየን እና በ2018 በጀት ዓመት 8.93 ቢሊየን የቤት ግብር መሰብሰብ ተችሏል።

የቤት ግብር አተገባበር በብር					
በጀት ዓመት	2014	2015	2016	2017	2018
አፈፃፀም	47.5 ሚ.	1.99 ቢ	7.73 ቢ	8.46 ቢ.	8.93 ቢ

የግብር ከፋዩን ቁጥር ከማሳደግ አንጻር በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት 182,842 ግብር ከፋይ በ2015 በጀት ዓመት ወደ 423,000፣ በ2016 በጀት ዓመት ወደ 502,289፤ በ2017 በጀት ዓመት 464,043 እንዲሁም በ2018 በጀት ዓመት ወደ 500,804 መረጃው እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ /እስከ ግንቦት/2018/ ግብር ከፋይ ማሳደግ ተችሏል

የቤት ግብር ከፋይ ቁጥር					
በጀት ዓመት	2014	2015	2016	2017	2018
አፈፃፀም	182,842	423,000	502,289	464,043	500,804

በአጠቃላይ የልማት ሀብት አቅርቦትን ከማሳደግ አንጻር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚቀርቡ የዋጋ ማሻሻያ ጥናቶች ጸድቀው ተግባራዊ በመደረጋቸው፣ የቤት ግብር ማሻያያ በመተግበሩ የገቢ አፈጻጸምን በልዩ ትኩረት በመገምገሙ የከተማው ሃብት አቅርቦት ዘላቂ ከመሆኑም ባሻገር በ2014 ከነበረበት ብር 70.45 ቢሊየን በ2018 ወደ 233.7 ቢሊየን መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን የ231.7 በመቶ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል። በአጠቃላይ በአምስት ዓመቱ ብር 856.25 ቢሊየን ታቅዶ ብር 826.57 ቢሊየን ወይም የዕቅዱን 96.53 % መሰብሰብ ተችሏል።

ዓላማ-2 ለዘላቂ ልማት የተመደበ የመንግስት በጀት በመቶኛ

ለዘላቂ ልማት የተመደበ በጀት በብር					
	2014	2015	2016	2017	2018
የፀደቀ በጀት በብር	69	98	152	241.95	350.13
ዘላቂ ልማትበብር	35.6	55.37	85.5	173.45	251.64

በመቶኛ	51.59	56.50	56.25	71.69	71.87

የተገኙ ውጤቶች

- **ይህ የተመደበው የዘላቂ ልማት በጀት በከተማ አስተዳደሩ የህ/ሰቡን የልማት ጥያቄ የመለሰ ሲሆን በተለይም ለስራ ፈላጊ ዜጎች ምቹ ሁኔታና ዘለቄታዊ የሥራ እድሎችን መፍጠሩ እና የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነትን በመከላከል ድህነትን መቀነሱ፣ የትምህርት ሽፋንና ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማደጉ፣ ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት ተደራሽነትን ማሻሻሉ፣ የመንግስት አገልግሎት መስጫ ተቋማት መገንባታቸውን አገልግሎት መስጠታቸው፣ አገልግሎትን አሰጣጥ መዘመኑ፣ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ማደጉ፣ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታና ሽፋንና ጥራት፣ መኖሪያ ቤቶች ግንባታና ፍትሃዊ ተደራሽነት ማደግ፣ ለከተማዋ ነዋሪዎች ዘላቂና አስተማማኝ ንፁህ የመጠጥ ውሃ መቅረቡ፣ የከተማው ሰላምና ጸጥታ መስፈኑ፣ የተማሪዎች ምገባ እና ሌሎች ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት የከተማውን ልማት ለማስቀጠል፣ ድህነትን በመቀነስ ልማትን ሊያረጋግጡ የሚያስችሉ ተግባራት ላይ ውሏል።**

ዓላማ-3 በጀት አጠቃቀም በመቶኛ

የከተማ አስተዳዳሩ በጀት ድልድልና አጠቃቀም በ2014 ከነበረበት 96% በ2018 ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 100% ማድረስ ተችሏል፣

ሠንጠረዥ 1. የጸደቀ በጀት

በጀት ዓመት	የተስተካከለ በጀት		ድምር	ድርሻ %	
	ለመደበኛ	ካፒታ		መደበኛ	ካፒታል
2014	35,781,394,762	34,888,821,265	70,670,216,027	51	49
2015	45,609,233,713	67,984,205,718	113,593,439,431	40	60
2016	57,401,234,136	104,629,954,360	162,031,188,496	35	65
2017	79,205,187,752	162,748,920,587	241,954,108,339	33	67
2018	107,361,670,697.15	252,709,390,430.85	360,071,061,128.00	30	70
ድምር	**289,613,107,692.91**	**622,961,292,361**	**948,320,013,421**	**34**	**66**

ምንጭ-የፋይናንስ ቢሮ IBEX መረጃ 2018 ዓ.ም

ምስል የበጀት ሂደቶች








በዚህም መሰረት የከተማ አስተዳደሩ የበጀት አጠቃቀም በ2014 97%፣ በ2015 101%፣ በ2016 105%፣ በ2017 100% እና በ2018 100% ማድረስ የተቻለ ሲሆን፤ አጠቃላይ የአምስት ዓመት አማካይ አፈጻጸም 100.75% ነው።

የተገኙ ውጤቶች

በጀትን በውጤታማነት በመጠቀም በከተማ አስተዳደሩ የልማትና መልካም አስተዳዳር ተግባራትን በተቀመጠላቸው ጊዜና ጥራት መሰረት የተፈፀሙ ሲሆን የመንግስት ተከፋዮች/ዕዳዎች ሳይሻገሩ ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

ዓላማ-4 የመንግስት ፕሮጀክቶች ፋይናንሻል አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ አፈፃፀም በመቶኛ

በአምስት ዓመት ውስጥ የመንግስት ፕሮጀክቶች ፋይናንሻል አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ አፈፃፀም 2014 ከነበረበት 98 % በ2018 በጀት ዓመት 100% ለማሳደግ ታቅዶ፤ በ2014 106.4%፣ በ2015 103.75%፣ በ2016 115.15%፣ በ2017 103.5% እና በ2018 155.7 % አፈጻጸሙን ማድረስ ተችሏል። የአምስት ዓመቱ አጠቃላይ አፈጻጸም 123.6% ሲሆን ከዕቅድ በላይ መፈጸም የተቻለበት ምክንያት የከተማ አስተዳደሩ የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ስራዎች በመከናወናቸው ነው።

ሠንጠረዥ 2.የጸደቁ እና ክትትልና ግምገማ የተደረገባቸው የመንግስት ፕሮጀክቶች

	የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት	ተግባሩ የተከናወነበት በጀት ዓመት						የ5 ዓመታት ድምር
			2014	2015	2016	2017	2018	
1	የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ተግባር በማከናወን ግብረመልስ መስጠት፤	እቅድ	1,000	1,200	1,320	1,229	1300	5761
		ክንውን	1,064	1,245	1,520	1,269	2025	7123
		አፈጻጸም %	106.4%	103.75%	115.15%	103.25%	155.7%	123.6%

ምንጭ-የፋይናንስ ቢሮ IBEX መረጃ 2018 ዓ.ም

የተመዘገቡ ውጤቶች

- ለተከታታይ 5 አመት ግንባታቸው በተለያየ ምክንያት የቆሙ 24 ፕሮጀክቶችን በመለየት የ16ቱን ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው የፕሮጀክት ባለቤቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራትና የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ፕሮጀክቶቹ ችግራቸው ተፈትቶ ወደ ተጠናከረ ግንባታ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፣

ለአብነት-የካ ወረዳ 03 ጤና ጣቢያ፣ ቦሌ ወረዳ 07 ጤና ጣቢያ ኮልፌ ወረዳ 14 ጤና ጣቢያ፣ አቃቂ ቃሊቲ ፖሊስ ጣቢያ፣ ኮልፌ ፖሊስ መምሪያ፣ ንፋስ ስልክ ፖሊስ መምሪያ፣ ልደታወረዳ 2 አስተዳደር ህንጻ፣ ንፋስ ስልክ ወረዳ 01 አስተዳደር ህንጻ፣ ንፋስ ስልክ እሳትና ድንገተኛ፣ ቂርቆስ ወረዳ 11 ጤና ጣቢያ፣ ቂርቆስ እሳትና ድንገተኛ ማስፋፊያ፣ ልደታ ፖሊስ መምሪያ ናቸው።

- ቅድመ ክፍያ ወስደው ወደ ስራ ያልገቡ ተቋራጮች የወሰዱትን ብር 306,107,947.84 በዳሰሳ ጥናት መረጃውን በማሰባሰብ በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ወደ ግንባታ ሂደት እንዲገቡ መደረጉ፣
- ግንባታቸው ከተቋረጡ ፕሮጀክቶች ሊመለስ የሚችል የመንግስት ሀብትን በተመለከተ የተደራጀ መረጃ በማሰባሰብ ሊመለስ የሚችልበትን አግባብ ምክረ ሃሳብ በማቅረብ ብር 8,037,329.17 ብር በድርድር እና በህግ ማስመለስ ተችሏል፣
- የግንባታ ሂደታቸው ተጠናቆ ወደ ስራ ያልገቡ 96 ፕሮጀክቶችን በተደረገው ክትትልና ድጋፍ ለአገልግሎት እንዲበቁ ማድረግ ተችሏል፣
- በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ የነበሩ ችግሮችን በቅንጅት ተጠንቶ አስተዳዳራዊ ውሳኔ እንዲሰጣቸው በማድረግ ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፣ ለአብነት ተቋርጠው የነበሩ የትራንስፖርት ስርአት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ወደተግባር ገብተዋል፤
- በመንገዶች ባለስልጣንና በትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽ/ቤት እየተሰሩ ለሚገኙ ፕሮጀክቶች የቀረቡ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ የመንግስትን እና የህዝብን ጥቅም ባስከበረ መልኩ መስተካከል እንዲችል በመረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ምክረ-ሃሳቦች ማቅረብ በመቻሉ ከብር 11,349,072,181.29 በላይ የመንግስት ሀብት ማዳን አስችሏል።
- ለ11ዱም ክፍለ ከተማ በተደረገ ክትትልና ድጋፍ መሰረት ከአረንጓዴ ልማት ጋር ተያይዞ በትክክል ልኬት ሳይወሰድና መልማቱ ሳይረጋገጥ ያለአግባብ ሊከፈል የነበረብር 19,728,810.38 ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት እና ከፋይናንስ ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት መስራት በመቻሉ ማዳን ተችሏል።
- ከዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ፣ እና ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር በመቀናጀት ለረጅም ጊዜ የግንባታ ሂደታቸው ቢጠናቀቅም ሌሎች ቀሪ ስራ ያላቸውን ችግር በማጥናትና አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በመደረጉ ፕሮጀክቶቹ ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። ለአብነት አቃቂ ፓርክ፣ ፈረንሳይ የህዝብ መዝናኛ ፓርክ፣ ራስሀይሉ የመዋኛ ገንዳ እና ሆላንድ ኢንባሲ የህዝብ መዝናኛ ፓርክ ናቸው።

ግብ-2 ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የተወጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ማሳደግ፣

ዓላማ-5. ክትትልና ድጋፍ የተደረገባቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክቶች በ2014 **በጀት ዓመት ከነበረበት** 78% **በ**2018 **በጀት ዓመት** 96% **ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ ከ**100% **ነው። ይህም ፕሮጀክቶችን ማበልጸግ፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ የፕሮጀክቶች ማጠቃለያ ግምገማ ማከናወንን ያጠቃልላል።**

- **ከ**2014 **እስከ** 2018 **በጀት ዓመት** 628 **ፕሮጀክቶችን ለማበልፀግ ታቅዶ** 660 **ፕሮጀክቶች ከመንግስት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አኳያ ተቃኝተው እንዲበለጽጉ ተደርጓል። በዚህም** 33.86 **ቢሊየን ብር የሚሆን ካፒታል የተመዘገበ ሲሆን** 5,771,770 **የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ተጠቃሚ ለማድርግ ስምምነት ተፈርሞ እየተሰራበት ይገኛል።**
- **ከ**2014 **እስከ** 2018 **በጀት ዓመት** 499 **የሲቨል ማህበረሰብ ድርጅቶች በፕሮጀክቶች ውል ስምምነታቸው መሠረት ማከናወናቸው በመስክ ክትትል እና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ** 512 **ፕሮጀክቶ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም** 103% **ነው። በዚህም** 9,442,072,521.26 **ብር ለ**1,514,355 **ተጠቃሚዎች በጤና፣ በትምህርት፣ አካልጉዳተኞች፣ ሴቶች እና ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋዊያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን በመቅረፍ መብትና ደህንነታቸውን በማስጠበቅ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።**
- **ከ**2014 **እስከ** 2018 **በጀት ዓመት በአምስት ዓመት ውስጥ** 528 **የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክት የመስክ ማጠቃለያ ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ** 531 **ፕሮጀክቶች የማጠቃለያ ግምገማ በማድረግ ግብረ መልስ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም** 100.4% **ሆኗል። በዚህም** 12,570,939,628.00 **ብር ለ**1,327,112 **ተጠቃሚዎች አካልጉዳተኞች፣ ህፃናት እና አረጋዊያን፣ በጤና፣ በትምህርት፣ ወጣቶችና ሴቶች በስራ እድል ፈጠራ ተጠቃሚ ተደርጓል።**

ሰንጠረዥ፦ ፕሮጀክት ማበልጸግ፣ ክትትልና ድጋፍ እና ማጠቃለያ ግምገማ፤

ተ.ቁ	ከ2014 እስከ 2018 /የ5 ዓመት/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አፈፃፀም				
	የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች	የፕሮጀክት ብዛት		የተመዘገበ ካፒታል በብር	የተጠቃሚ ብዛት
		እቅድ	ክንውን		
1	ፕሮጀክት ማበልፀግ	628	660	33.86 ቢሊየን	5,771,770
2	ፕሮጀክት ክትትልና ድጋፍ	499	512	9.44 ቢሊየን	1,514,355
3	ፕሮጀክት ማጠቃለያ ግምገማ	528	531	12.57 ቢሊየን	1,327,112

የሲማድ ከ2014 እስከ 2018 የአፈፃፀም ሪፖርት						
	2014	2015	2016	2017	2018	ድምር
ፕሮጀክት ማበልፀግ	132	133	125	132	138	660
ፕሮጀክት ክትትልና ድጋፍ	102	101	101	105	104	513
ፕሮጀክት ማጠቃለያ ግምገማ	104	105	106	106	110	531
ዘላቂ ገቢ ማስገኛ ማካተት	15	16	14	20	22	87
ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ	13	14	15	19	20	81

- **ተደራሽ የተደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች በተደረገው ፕሮጀክት ማበልፀግ፣ ክትትልና ድጋፍ እና የማጠቃለያ ግምገማ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ አገልግሎት አካል ጉዳተኞች (People with disabilities)፣ ተማሪዎች፣ ሴተኛ አዳሪዎችና ለሴተኛ አዳሪነት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች፣ ወጣቶች፣ ጥቃት የደረሰባቸውን እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች (ሴቶችና ሕፃናት)፣ ለስደት ተጋላጭ የሆኑ፣ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች፣ በደማቸው ኤች አይ ቪ ቫይረስ የሚገኝባቸው ዜጎች እና ለኤች አይ ቫይረስ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ተንከባካቢ የሌላቸው ህጻናት የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ሆነዋል።**
- **በማህበራዊ ዘርፍ የተሰጡ አገልግሎቶች የስነ ልቦናዊ ድጋፍ ፣ሕፃናትን ወደ ቤተሰቦቻቸው የማቀላቀል፣ የአደራ ቤተሰብ አግልግሎት ፣የተቋም አገልግሎት**

(አረጋውያንና ሕፃናት)፣ በቡድን ቤት (Group home)፣ ጉዲፈቻ ቤተሰብ ፣ ጊዜያዊ የመጠለያ ድጋፍ /rehabilitation/፣ የህፃናት የቀን መዋያ አገልግሎት (Day care service)፣ ቤሰብ ማቀላቀል፣ የምገባ አገልግሎትና ምግብ ነክ እደላ የመኖሪያ ቤት እና የመፀዳጃ ቤት ግንባታና እድሳት የቤት ኪራይ ገንዘብ ድጋፍ የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ፣ ለተጠቃሚዎቻቸው የጤና ሁኔታቸውን የመከታተል /ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች/፣ የጤና አገልግሎት፣ ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እና የአልባሳት ድጋፍ፣ የስልጠና እና የቀጥታ የምግብ ድጋፍ፣ የስነ-ተዋልዶ ጤና የማማከር አገልግሎት፣ የአዕምሮ ጤና ሕክምና እና የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል።

ምስል 1. የቤት ዕድሳት



- የአእምሮ እድገት ውስንነት እና የኦትዝም ችግር ላለባቸው ህፃናት የፊዝዮተራፒ አገልግሎት እና ስልጠና ፣

ምስል 2. የአዕምሮ ውስንነት ያለባቸው ምርቃት



- በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት የልብና የኩላልት ቀዶ ጥገና፣ የሳምባ፣ የካንሰር ታማሚዎች፣ ኤች አይ ቫይረስ በደማቸው የሚገኝ እና ለሎች ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከል እና ድጋፍ በማድረግ ወደ መደበኛ ህይወታቸው እንዲመለሱ ተደርጓል።

ምስል 4 የህክምና አገልግሎት



ትምህርት ቤት በመክፈት ለተማሪዎች ነጻ የምገባ ፣ የንጽህና መጠበቂያ ፣ የዩኒፎርም እና የትምህርት መሳሪያዎች ድጋፍ ተደርጓል፣ የማጠናከሪያ ትምህርት ድጋፍ የትራንስፖርትና የትምህርት ቤት ክፍያ እና ነፃ የትምህርት በትምህርት ቤቶች ላይብረሪ በመገንባትና አስፈላጊ ግብዓቶች ድጋፍ በማድረጉ ተማሪዎች ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ አስችሏል፣

ምስል 5. የትምህርት ግብአት ድጋፍ የተደረገላቸው ተማሪዎች፤



❖ በትምህርት ቤቶች መጸዳጃ ቤቶችን በመገንባት፣ በማደስና በማስዋብ ምቹ የመማር ማስተማር ቦታ ተዘጋጅቷል።

ምስል.6.የሴትና የወንድ ተማሪዎች መፀዳጃ ቤቶች



❑ ለአካል ጉዳተኞች የስነልቦና ምክር አግልግሎት፣ የፊዙተራፒ፣ የዊልቼር እና አጋዥ መሳሪያዎችን ድጋፍ በማድረግ ያለ ረዳት እንዲመገቡ፣ የአልባሳት፣ የህክምና እና የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፤

ምስል 7. ለአካ ጉዳተኞች የመንቀሳቀሻ ዊልቸር ድጋፍ



- ለዓይነ-ስውራን የስነ ልቦና የምክር አገልግሎት በመስጠት የብሬል እና የኮምፒውተር ጃዉስ መጠቀም እንዲችሉ እና ማንኛውንም ሥራ መስረት የሚያስችላቸው ምቹ ሁኔታዎችን እዲፈጠርላቸው ተደርጓል፣

ምስል 8. ለአይነስውራን የብሬል ስልጠና እና ምርቃት ፕሮግራም፤



- በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት አመራሮች፣ ባለሙያዎችና መምህራን የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።
- መስማት የተሳናቸው ሕፃናት እና አሳዳጊዎቻቸው የምልክት ቋንቋና የመስማት አጋዥ መሳሪያዎች (Assistive Devices) ትምህርት ቤት በመክፈት እና የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደርጓል፣

ምስል 9. በትመህርት ላይ ያሉ መስማት ተሳናቸው ህጻናት፤



- ረዳት የሌላቸው አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማንን በተቋም ድጋፍና እንክብካቤ የስነ ልቦናና የምክር አገልግሎት በመስጠት እንዲጠሩ ከማድርግ በተጨማሪ የገንዘብ፣ የምግባ አገልግሎት፣ ጊዜያዊ መጠለያ እና የተለያዩ የጤና ድጋፎችን እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

ምስል 10. ረዳት ለሌላቸው አረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን በምግባ ላይ ያሉ፤



በከተማ አስተዳደሩ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተሰጡ ድጋፎች

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እየናረ የመጣውን የቢሮ እና የአግልግሎት መስጫ ተቋም ክራይ፣ ጫና ለማቃለልና በህብረተሰቡ ስም የተሰበሰበውን ሀብትና ንብረት በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ማዋል እንዲችሉ ውስን የሆነውን የከተማ መሬት ከ2014 እስከ 2018 ዓ.ም 148,123 ካ.ሜ የሚሆን ይዞታ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

ተሰጥቷል።

- ከ2014 እስከ 2018 በጀት ዓመት ውስጥ ከከተማ አስተዳደሩ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለበጎ አድራጎት አገልግሎት የተሰጡ ይዞታዎችን ለታለመለት ዓላማ መዋሉን 80 በመስክ ክትትል ለማድርግ ታቅደው 200 ይዞታዎች ላይ ክትትል ለማደረግ ተችሏል። ለዚህ አፈፃፀም ከፍ ማለት ምክንያት የሆነው ቢሮ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከማእከል እስከ ወረዳ ያሉ የመንግስት መዋቅር በመጠቀም በተለያዩ ጊዜያት ለሲማድ የተሰጡ ይዞታዎችን የመለየትና የማጥራት ስራ በመከናወኑ ነው። በዚህም 31 የሰንድ አልባ ይዞታዎችን ማግኘት የተቻለ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በፋይናንስ ቢሮ ስም እንዲዘጋጅ ከወረዳ ሰነድ እንድደራጅ በማድረግ ወደ ክ/ከተማ እንዲላክ ተደርጓል። ክ/ከተማ ሰነዶቹን ስካን በማድርግ ወደ ማእከል በኦን ላይን እንድላክ ተደርጎ ካርታ ለማውጣት ቢደት ላይ ይገኛል።
- ከተማ አስተዳደሩ በተለያዩ ጊዜ የተሰጡ ይዞታዎችን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በፋይናንስ ቢሮ ስም ለማስመዝገብ 18 ታቅዶ 20 ይዞታ በፋይናንስ ቢሮ ስም እንድመዘገብ ተደርጓል። በዚህም ውስን የሆነውን የከተማ መሬት ከሌብትና ብልሹ አሰራር በመከላከል ይዞታው ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ተደርጓል።

በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተሰጡ አገልግሎቶች የተገኙ ውጤቶች

- አካል ጉዳተኞች ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማግኘታቸው ራሳቸው እንዲችሉና በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ችለዋል፣
- ሴቶች እና ወጣቶች የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡና የስራ እና የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ችለዋል፣
- የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ የሙያ እና የክህሎት ስልጠና ወስደው የራሳቸውን ስራ በመፍጠርና ገቢ በማመንጨት በኢኮኖሚ ራሳቸውን ለማስተዳደር ችለዋል፣
- አረጋውያን መሰረታዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት የቀጥታ ድጋፍ ማግኘት ችለዋል፣
- ለሕጻናት የተለያዩ ድጋፎችን በማድርግ መብት እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ተደርጓል ፣
- ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የመከላከል ስራ በመሰራቱ የበሽታዉ ስርጭት እንዲቀንስ አስተዋጽዖ ለማድረግ ተችለዋል፣

- የምግብ እጥረት በእናቶች እና በሕጻናት ላይ እንዳይከሰት በአመጋገብ ዙሪያ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋጽያ አበርክተዋል፣
- በስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ የግንዛቤ እና ስልጠና ስራ በመሰራቱ የአመለካከተ ለውጥ ማምጣት ተችለዋል፣
- ለሕክምና ወደ ውጭ አገር በመሄድ የሚወጣውን ወጪ እና እንግልት ለመቀነስ አስተዋጽያ ተደርጓል፣
- የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ የሙያ እና የክህሎት ስልጠና ወስደው የራሳቸውን ስራ በመፍጠርና ገቢ በማመንጨት በኢኮኖሚ ራሳቸውን ማስተዳደር ችለዋል።

ዓላማ-6 በዘላቂ የገቢ ማስገኛ መስክ ተጠቃሚ ያደረጉ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

በ2014 ከነበረበት 30/12%/ በ2018 37/15%/ለማድረስ ታቅዶ ክንውኑ 47/19%/ ማድረስ ተችላል።

በኢኮኖሚ ዘርፍ

- ከ2014 በጀት ዓመት እስከ 2018 በጀት ዓመት በዓመት በ5 ዓመት ውስጥ መሠረታዊ የንግድ ክህሎት እና የሙያ ስልጠና በመስጠት የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ እንዲሰማሩ የፕሮጀክት ስምምነት ከፈፀሙ ድርጅቶች ውስጥ በውላቸው መሠረት ለተጠቃሚዎች ድጋፍ ማድርጋቸውን ለማረጋገጥ 64 ታቅዶ 81 /126%/ ፕሮጀክቶች ላይ ተከናውኗል። በዚህም 10,571 የሚሆኑ ሴቶች እና ወጣቶች የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት መነሻ ካፒታል 264,505,500.00 ብር የስራ ማስጀመሪያ ድጋፍ በማድርግ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው እና በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ተደርጓል።

❖ የብረታ ብረት ስራ፣የግንባታ ስራ ማጠናቀቂያ፣ እና ለሎች የተለያዩ ስልጠና በመስጠት ስራ እድል እንዲፈጠርላቸው በማድረግ በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ተደርጓል።

ምስል 11. በብረታ ብረት ስራ እና እንጀራ በመጋገር ላይ የተሰማሩ፤





❖ በተጠቃሚዎች የገበያ ፍላጎት ላይ በመመስረት የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ስልጠናዎችን፣ በምግብ ዝግጅት እና የሆቴል አስተዳደር፣ የአሸከርካሪነት የሙያ ብቃት፣የእንጨት ስራ፣

ምስል 12. የሆቴል ሙያ ስልጠና በመውሰድ ወደስራ የተሰማሩ፤




ለምስል 13. የከተማ ግብርና




➢ በከተማ ግብርና አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት በዶሮ እርባታ፣ በጓሮ አትክልት ምርት የላም ወተት ላይ ተሳትፈዋል። ለዚህም ለአንቀሳቃሾች የግብይት ትስስር ተፈጠሮላቸው ሴቶች እና ወጣቶች በየራሳቸው ስራ እንዲሰማሩ ለማድርግ ተችሏል።

ምስል14. ከስደት ተመላሾች የስነልቦና ምክር አግልግሎትና የተለያዩ የሙያ ስልጠና በመስጠት ስራ እንዲል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል።



ግብ-3 የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፣

ዓላማ-7. ዓመታዊ ሂሳባቸውን እስከ ነሐሴ 20 የዘጉ ተቋማት ቁጥር በ2014 ከነበረበት 96% በ2018 በጀት ዓመት 100% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 100 % ነው፣

የክፍያ ዓፈጻጸም በ2014 ብር 67.88 ቢሊየን /96 %/፣ በ2015 በብር 102.9 ቢሊየን /90.6%/፣ በ2016 ብር 155.72 ቢሊየን /96.10%/፣ በ2017 ብር 227.50 ቢሊየን /94 %/ እና በ2018 (የ10 ወሩ) ብር 276.3 ቢሊየን ሲሆን አፈፃፀሙም 77.10% ነው። በ5 ዓመቱ ብር 830.30 ቢሊየን / 87.70/ ክፍያ ተፈጽሟል፣

ከ2014 እስከ 2018 የተስተካከለ በጀት በቢሊየን			
በጀት ዓመት	**የወጪዕቅድ**	**አፈጻጸም**	**በ%**
2014	70,670,216,028.00	67,877,738,876.60	96.00%
2015	113,593,439,432.17	102,898,738,677.15	90.60%
2016	162,031,188,497.01	155,725,923,864.76	96.10%
2017	241,954,108,339.87	227,493,973,326.99	94%
2018 /11ወር/	358,256,650,708.57	284,520,297,944.85	77.10%
ከ2014-2018	946,505,603,005.62	830,252,279,203.30	87.70%

ሂሳብ አዘጋግን በተመለከተ፤

- **ሂሳብ አቅራቢ መስሪያ ቤቶች ቁጥር በየበጀት ዓመቱ የተለያየ ቢሆንም በፋይናንስ አስተዳዳር ደንብና መመሪያ መሰረት ሂሳባቸውን በ5ቱም ዓመታት በመስከረም ወር ውስጥ ዘግተዋል፣**
- **በሂሳብ አዘጋግ የመጡ ውጤቶችን በተመለከተ፤**
- **ከ2014 በጀት ዓመት እስከ 2017 በጀት ዓመት ድረስ ያለው ሂሳብ በወቅቱና በጥራቱ በመዘጋቱና አዲት በመደረጉ፣**
- **ከ2014 በጀት ዓመት እስከ እስከ 2017 በጀት ኣመት ያለው ሂሳብ በመንግስት ሂሳብ መመሪያው መሰረት ሂሳባቸውን በወቅቱ በመዝጋት የተዘጋውን የሂሳብ ሪፖርት ለፌደራል ገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ**

ጽ/ቤት እና ለአዲስ አበባ ዋናው ኦዲተር ቢሮ በወቅቱ የተላከ ሲሆን የተጠቃለለውም የሂሳብ ሪፖርት በየበጀት ዓመቱ ኦዲት ተደርጓል።

ዓላማ-8. የቀነሰ ውዝፍ፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች በመቶኛ

- ውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂቦችን ማስቀነስ በተመለከተ በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት 25% በ2018 ወደ 38% ለማስቀነስ ታቅዶ 30.4%/101% ማሳካት ተችሏል። በዚህ መሰረት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በ2014 20%/81%/ በ2015 23% /82%)፣ በ2016 22% /75%)፣ በ2017 /33%/ 87%) እና በ2018 38 % /82%/ እንደየቅደም ተከተላቸው መቀነስ ተችሏል።

የቀነሰ ውዝፍ፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች			
በጀት ዓመት	ዕቅድ	ክንውን	በ%
2014	4,734,556,227.41	3,841,448,263.0	81%
2015	6,314,948,675.12	5,612,133,242.09	82%
2016	10,275,232,634.12	7,706,424,755.61	75%
2017	15,459,468,677.63	13,409,880,559.29	87%
2018	14,802,005,001.41	15,459,002,241.69	101%

ዓላማ-9- የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የተገበሩ ተቋማት ሽፋን በመቶኛ

- የፋይናንስ አሰራር ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የተገበሩ ተቋማትን በ2014 ከነበረበት 25 % በ2018 ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 100% ተከናውኗል። በየደረጃው ላሉ የምክር ቤት አባላት በአስፈጻሚ ተቋማት ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ማደረግ እንዲችሉ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳዳር ላይ /በበጀት አስተዳደር፣ በመንግስት ሂሳብ አያያዝ፣ በግዥና ንብረት አስተዳደር/ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፣

በመንግስት በጀት ምንነት እና አዘገጃጀት ላይ በሁሉም ወረዳዎች ላለፉት አምስት ዓመት ያለማቋረጥ በየወረዳው ለ50 ዜጎች፣ የተመደበ በጀት የበጀት አፈጻጸም የግዥ ሂደትና የኦዲት መረጃዎችን ለነዋሪው ህበረተሰብ ተደራሽ በማድረግ ህብረተሰቡ የዓመታዊ በጀት አፈጻጸምን፣ የመንግስት ግዥ ሂደትንና የአገልገሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን በመገምገም ጠያቂ ህብረተሰብ ለመፍጠር ተችሏል። በተጨማሪም በሁሉም ወረዳ ህብረተሰቡ በቅድመ በጀት ውይይት ላይ እንዲሳተፍ በማድረግ በበጀት አመዳደብ ላይ አሳታፊነትን መፍጠር ተችሏል።

የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር /የበጀት አስተዳደር፣ የጥሬገንዘብ አስተዳደር፣ የመንግስት ግዥ አፈጻጸምና የመንግስት ሂሳብ አያያዝ/ አፈጻጸምን በአግባቡ ለመገምገም የሚያስችሉ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማዘጋጀት በሁሉም ወረዳዎች ምዘና ተካሂዷል።

የዜጎች የበጀት መረጃ /Citizen Budget/ ሰነድ ከ2014-2018 በማዕከል በክ/ከተማና በወረዳ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለህብረተሰቡ ተደራሽ በመደረጉ በጀትን በተመለከተ መረጃ ለሚፈልጉ አካላት ቀለል ባለ ዘዴ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።


ማህበራዊ ተጠያቂነት

በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሲሰራ የነበረው የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ የከተማ አስተዳደሩ እንዲያስቀጥል በተወሰነው መሰረት አገልግሎት ተቀባዩ ህብረተሰብ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን በመፈተሽና በመመዘን ችግሮችን ለይቶ ከአገልግሎት ሰጪ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ የጋራ በማድረግ የተለዩትን ቅደሚያ የሚሰጣቸውን ችግሮች ለመፈታት የጋራ የድርጊት መረሃ ግብር በማዘጋጀት በሙከራ ደረጃ በተመረጡ 26 ወረዳዎች በሚገኙ 28 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ለማሳደግ በድምሩ ከ3.6 ቢልየን ብር በላይ በማስመደብ የG+2 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መማሪያ ክፍሎች፣ የG+4 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ፤ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ግንባታ፣ የመዋለ ህጻናት ማሸለቢያ ግንባታ፣ የመጸዳጃ ቤት ግንባታና ጥገና፣ የቤተ-ሙከራ፣ የመማሪያ እና ቤተ-መጽሃፍትና የICT ክፍል ግንባታና ግብዓት ማሟላት፣ ሁለገብ አስተዳደር ህንጻ ግንባታ፣ የምድረ-ግቢ ማስዋብ፣ የመጫወቻ ሜዳ እና አጥር ግንባታ እና የትራንስፎርመር ግዥ ስራዎች ለአብነት ይጠቀሳሉ።

በማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት የተለዩና ከአገልግሎት ሰጪ አካላት ጋር

የጋራ ተደርገው የድርጊት መርሃ ግብር የተዘጋጀላቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ አቅርቦት ክፍተቶች በFTA-SA-GRM የትስስር በመገምገም በዕቅዱ መሰረት በአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ያልተፈቱ ጉድለቶችን በመለየት ክፍተቱ እንዲሞላ ማድረግ ተችሏል።

ምስል 14 ልዩ ልዩ ግንባታዎች እና የግብዓት ድጋፍ
















menu for current window
ns Start menu
e through property tabs
cel last function









በ2014 በቻናል አንድ ፕሮግራሞች ለከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ከተደለደለው ብር 3,147,055,234.00 ታቅዶ የተፈፀመ ክፍያ 1,742,265,707.48 ወይም 55.36%፣ በ2015 ለስራ ፈጠራ UPSNJP ፕሮጀክት የብር 1,022,561,837.62 ክፍያ ለመፈጸም ታቅዶ፤ ብር 956,518,162.11 የተከፈለ ሲሆን አፈፃፀሙም 93.54% ነው። በ2016 በጀት ዓመት በስራ ፕሮግራም /UPSNJP/ ከተመደበው በጀት ውስጥ ብር 3,463,909,989.51 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች የተለያዩ ክፍያዎች እና ለካፒታል ስራዎች ብር 2,575,642,167.16 ክፍያ ተፈጽሟል። ለከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት በ2017 ብር 3,350,111,970.00 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 3,176,964,477.00 /94.8%/ እና በ2018 /10 ወራት/ ብር 2,664,003,242.28 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 2,335,105,341.00 /87.65%/ ለመጠቀም ተችሏል።

የከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተለያዩ የገንዘብና የሂወት ክህሎት ድጋፎችን በማድረግ በዘላቂነት ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ተጠቃሚዎች ለሶስት ዓመት በፕሮግራሙ ታቅፈው እንዲቆዩ በማድረግ በቆይታቸው ራሳቸውን ለመቻል የሚያስችላቸው የተለያዩ ስልጠናዎች እና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ገቢያቸውና ኑሯቸው እንዲሻሻል ማድረግ ከመቻሉም በተጨማሪ የመጀመሪያው ምዕራፍ አፈጻጸም አመርቂ በመሆኑ ለሁለተኛው ምዕራፍ የዓለም ባንክ ድጋፍ ብድር መሆኑ ቀርቶ ወደ ድጋፍ እንዲቀየር ምክንያት ሆኗል።

ምስል 16. የመስሪያ ማሳያ እና መሸጫ ህንጻዎች




በሀገር ደረጃ በተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ከመንግስት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በከተማ ደረጃ ጥር /2017 ዓ.ም/ ተግባረዊ ተደርጓል። በዚህም መሰረት

በቀጥታ ድጋፍ 24,788 እንዲሁም በአካባቢ ልማት 130,135 በድምሩ 154,923 በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የከተማችን ነዋሪዎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በከተማችን በአምስቱም የአካባቢ ልማት ስራዎች ማለትም በበደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በውበትና አረንጓዴ ልማት፣ በአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ፣ በከተማ ግብርና ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንዲሁም በአነስተኛ የመሠረተ ልማት ስራዎች ላይ በመሳተፍ ከተማችን ውብና ጽዱ እንድትሆን ለማድረግ በአካባቢ ልማት ስራ የተሰማሩ የስራ ሃይሎች በቀን 4 ሰዓት ሰርተው በቀን ለአንድ ተጠቃሚ 203 ብር የሚከፈላቸው እና የቆይታ ጊዜአቸውም ለሶስት አመታት ሲሆን የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ደግሞ ለአንድ ተጠቃሚ በወር 589 ብር የሚከፈላቸው ሆኖ አንድ ቤተሰብ እስከ አራት የቤተሰብ አባል ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል ሲሆን /አራት የቤተሰብ አባል ያለው የአከባቢ ልማት ተጠቃሚ በወር 203 ብር * 4ቀን * 4 ሰራ ሃይል=3,248.00 ብር ድጋፍ ያገኛል።

ምስል 17. የአካባቢ ልማት ስራዎች





ይህ በአካባቢ ልማት ስራ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች ከሚከፈላቸው ክፍያ 20% በመቆጠብ የህይወት ክህሎት ስልጠና፣ በመረጡት የሙያ መስክ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ገብተው የቴክኒካል ስልጠናዎችን፣ በንግድ እቅድ እና ገንዘብ አያያዝ ስልጠናዎች የሚሰጣቸው ሲሆን፣ አዋጭ እና አቅማቸውን ያገናዘበ የንግድ እቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ እና 600 ዶላር የስራ ማስጀመሪያ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጣቸው ይሆናል፣

የአጠቃላይ ትምህርትጥራትን ማሻሻያ በተመለከተ

ለ2014 በጀት ዓመት የተደለደለውን ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም /GEQIP/ 55.5 ሚልየን ብር 100%፣ በ2017 በጀት (GEQIP) ለበጀት

ዓመቱ ከተመደበው 4,696,846.00 ውስጥ ብር 4,119,502.00 (88%) ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተላልፏል።

ፕሮግራሙ በትምህርት ጥራትና አሰጣጥ ደረጃ ማሻሻያ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ባለፉት አራት አመታት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ 336 ት/ቤቶች ከትሬዥሪና ከውስጥ ገቢ ምንጭ ከሚመደብላቸው በጀት በተጨማሪ ከአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የSchool Grant በጀት እየተለቀቀላቸው እንደ ትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ የትምህርት ጥራት ጥራትን ከማሻሻል አንጻር ለሚያስፈልጉ ቁሳቁስና ግብአት ግዥ እንዲውል ተደርጓል። በተጨማሪም COVID-19 ስርጭትን ለመከላከል በ የክፍለ ከተማው በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የእጅ መታጠብያ ግንባታ እና የውሃ ማጠራቀሚያ ግዥና ተከላ በማካሄድ የኮቪድ ስርጭትን ለመከላከል የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

ምስል 18 ልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ግንባታዎች




የSchool Grant በጀት ከሚለቀቅላቸው 336 ት/ቤቶች በተጨማሪ በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በኩል 556 ትምህርት ቤቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድጋፎች በማድረግ የአንዥር መጻህፍት ህትመት፣ የመምህራን አቅም ማሳደግ፣ለአካቶ ትምህርት አሰጣጥ አጋዥ መሳሪያዎች ድጋፍ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን በማሳደግ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

ዓላማ-10. IBEX ተጠቃሚ ተቋማት በመቶኛ

IBEX ተጠቃሚ ተቋማት 100% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 100% ነው። ይህም ከተቋማት የቀረቡ ጥያቄዎች በሙሉ ምላሽ እንዲሰጣቸው በመደረጉ ነው።

- በ2014 በጀት ዓመት IBEX ተጠቃሚ 89፤ በ2015 በጀት ዓመት 41፣ በ2016 በጀት

ዓመት 60፣ በ2017 በጀት ዓመት IBEX ተጠቃሚ 21፣ እና በ2018 በጀት ዓመት 64 ተቋማት በድምሩ 275 ተቋማት በ5 ዓመቱ የIBEX System ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው።

- ተቋማት የተቀናጀ የበጀት እና ወጪ ስርዓትን በመጠቀማቸው የበጀት ድልድልና አስተዳደር ቀልጣፋ እንዲሆን፣ የሂሳብ አያያዝ ስርአቱን የተከተለ እንዲሆን፣ ሪፖርቶችን በወቅቱና በጥራት ማውጣት ማስቻሉ፣ የወረቀት ስራ እንዲቀንስ ማስቻሉ፣ የበጀት አስተዳደር ስርአት የተቀላጠፈ እንዲሆን ማድረጉ፣ የሂሳብ ስራዎችና የበጀት ቁጥጥር ግልጸኝነት እንዲሰፍን ማደረጉ፣ የመረጃ ተደራሽነት እና አያያዝ አስተማማኝ እንዲሆን አስችላል።

ዓላማ-11 ዘመናዊ የደሞዝ ክፍያ/ITAP/ ተጠቃሚ ተቋማት በመቶኛ

ዘመናዊ የደሞዝ ክፍያ/ITAP/ ተጠቃሚ ተቋማት ከ2014 እስከ 2018 በጀት ዓመት 100% ለማድረስ ታቅዶ 100% ተከናውኗል። ይህም ከተቋማት የቀረቡ ጥያቄዎች በሙሉ ምላሽ እንዲሰጣቸው በመደረጉ ነው።

- በ2014 በጀት ዓመት ለ51፣ በ2015 በጀት ዓመት ለ90፣ በ2016 በጀት ዓመት ለ53፣ በ2017 በጀት ዓመት ለ21 እና በ2018 በጀት ዓመት ለ49 ተቋማት በድምሩ 264 ተቋማት በ5 ዓመቱ የiTap System ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው።

በዚህም መሰረት ተቋማት የሰራተኞችን የስራ ሰዓት መግቢያ እና መውጫ ለመቆጣጠር፣ የደመወዝ ክፍያ ክፍተትን ለመዝጋት፣ በብልሹ አሰራርና የመልካም አስተዳደር ግድፈቶች ምክንያት ሊባክን የነበረውን የመንግስት ሀብት በማዳን ለልማት እንዲውል ተደርጓል።

ዓላማ-12. ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት ያቀረቡ መስሪያ ቤቶች በመቶኛ

- ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት ያቀረቡ መስሪያ ቤቶች በ2014 ከነበረበት 15% በ2018 85 % ለማድረስ ታቅዶ፤ አፈፃፀሙ በ2014 20%፣ በ2015 77 %፣ በ2016 81.6% በ2017 82% እና በ2018 85% ማከናወን ተችሏል። አፈፃፀሙ 100% ነው፤

ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት እቅድ ክንውን					
	2014	2015	2016	2017	2018
እቅድ	15%	75%	81%	82%	85%
ክንውን	20%	77%	81.6%	82%	85%

አፈጻጸሙ ከ100% በላይ የሆነበት ምክንያት በጥቆማ የሚቀርቡ እና በትዕዛዝ የተከናወኑ የኦዲት ስራዎች በመኖራቸው ሲሆን፤ የተቋማትን የውስጥ ኦዲት የስራ ክፍሎችን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ በመስጠት፣ የኦዲት ጥራት ሪፖርት በመገምገም፣ የጋራ ምክክር ጉባዔ እና የተዘረጋውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ፣ ደንብና መመሪያውን ተከትሎ ባልፈፀሙ እና የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል በማድረግ፣ የጥቆማ ኦዲት በማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል በማድረግ፤ የፈሰስ ሂሳብና የንብረት ቆጠራን ክትትል ግብረ መልስ በመስጠት፤ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና በመስጠት ነው።

የተገኙ ውጤቶች

- የውስጥ ኦዲት የአሰራር ችግሮችን በመፈተሽ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እንዲሰራ በጤና ጣቢያና በት/ቤቶች የነበሩ የውስጥ ኦዲት አደረጃጀቶችን ወደ ወረዳ በክፍለ ከተማ ፑል ስር የነበሩትን ወደ አንድ በማምጣት በክ/ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት ስር እንዲደራጅ በማድረግ የውስጥ ኦዲቱ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እንዲሰራ አድርጎታል።
- በየመ/ቤቱ የሚገኙ የውስጥ ኦዲተሮችን አቅም በመገንባት በአምስት ዓመቱ ውስጥ ለ1028 የውስጥ ኦዲተሮች ተቋማዊ ስልጠና በመስጠት የኦዲት ስራው በጥራት በጊዜና በመጠን እንዲከናወን ማድረግ ተችሏል።
- የውስጥ ኦዲተሮችን ችግሮች ለመፍታት እና አሰራሮችን ለማሻሻል በዓመት ሁለት ጊዜ ውይይት በማድረግ፣ በየበጀት ዓመቱ ከማዕከል እስከ ወረዳ ለሚገኙ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፤ ለአመራሩ ግንዛቤ በመስጠት ከኦዲት ተደራጊዎች እና በተወሰኑ አመራሮች የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለአብነት ምቹ የስራ አካባቢና ቢሮ ግብዓት የሌላቸው፣ ሰነድ አለማቅረብ፣ የመውጫ ውይይት ላይ አለመገኘት ለኦዲት ስራው ክፍተት የሚሆኑ ጉዳዮች እንዲፈቱ በማድረግ ውጤቶች ተመዝግበዋል።
- የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን ከማጠናከር አንፃር በአምስት ዓመት ውስጥ 242 መ/ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም ለመንግስት ሀብት ብክነት ምክንያት ወይም ስጋት የሆኑትን በመለየት ግብረመልስ በመስጠት በአሰራር ስርዓቱ ላይ የሚታዩ ስጋቶችን መቀነስ ተችሏል። ለአብነት ቼክ በፊራሚዎች እጅ ይቀመጥ የነበረውን እንዳይቀመጥ በማድረግ፣ አንድ ቁልፍ ሁለት የንብረት ክፍል ሰራተኞች እንዳይጠቀሙ በማድረግ ዋስ ማቅረብ ያለባቸው ስራተኞች ዋስ እንዲያቀርቡ በማድረግ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ እንዲጠናከር እና የመንግስት

ሀብት ከብክነት ለማዳን ተችሏል።

- ደንብና መመሪያውን ተከትሎ ባለመፈፀሙ የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል ከማድረግ አንፃር የኦዲት ፎረም በመቋቋሙ በፎረሙ አማካኝነት ንቅናቄ በመፍጠር እና ግንዛቤ በመስጠት ግኝት እንዲመለስ መደረጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል። በዚህ መሰረት፤
    - በ2014 በጀት ዓመት ብር 12,997,584.52
    - በ2015 በጀት ዓመት ብር 20,613,339.81
    - በ2016 በጀት ዓመት ብር 23,304,473.87
    - በ2017 በጀት ዓመት ብር 347,522,492.81
    - በ2018 **በጀት ዓመት ብር 200,300,278.28**

  በድምሩ 592,359,868.73 በመደበኛ፣ ጥቆማ እና በዋና ኦዲተር በተሰሩ የኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል።
- በ5 ዓመቱ /ከ2014-2017/ በጀት ዓመት ሂሳብ መዝጊያ በ393 የማዕከል መ/ቤቶችን የፈሰስ ሂሳብና የንብረት ቆጠራን ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ ለመስጠት ታቅዶ፤ በ393መ/ቤቶች ክትትል ድጋፍ ተደርጎ ግብረ መልስ ተሰጥቶ የሁሉም መ/ቤቶች የፈሰስ ሂሳብ በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ በመጣው መሰረት ማጣራት ተደርጎ በ2014 ብር 109,366,700.95 ፣ በ2015 ብር 50,672,105.51 በ2016 ብር 131,131,050.24 እና በ2017 ብር 337,599,710.30 በጀት እንዲቀነስ ለሚመለከተው ተገልጿል።

ዓላማ-13. ከሚፈጸሙ የመንግስት ግዢዎች የግልፅ ጨረታ ድርሻ በመቶኛ

ከሚፈጸሙ የመንግስት ግዥዎች የግልፅ ጨረታ ድርሻ በ2014 ከነበረበት 70% በ2018 በጀት ዓመት 72% ለማድረስ ታቅዶ፤ አፈጻጸሙ 68 /94%/ ማድረስ ተችሏል፣ በዚህም መሰረት የግልፅ ጨረታ ድርሻን በ2014 በጀት ዓመት 80%፣ በ2015 በጀት ዓመት 70%፣ በ2016 በጀት ዓመት 68%፣ በ2017 በጀት ዓመት 68% እና በ2018 በጀት ዓመት 66.5% ማድረስ ተችሏል። የአምስት አመቱ አማካይ አፈጻጸም 70.5% መሆኑን ያመላክታል፣ ይህ የሆነበት ምክንያት በ2016፣ በ2017፣ በ2018 በጀት ዓመት ከተማዋ በኮሪደር ልማትና ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑ የልማት ስራዎች ለሚያከናውኑ ተቋማት ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ፣ መንገዶች ባለስልጣን፣ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ ትላልቅ ፕሮጀክትቶች ጽ/ቤት፣ ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፣ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን፤ የሲቪል ምዝገባና ነዋሪዎች መረጃ ባለስልጣን፣

እንዲሁም 11 ክ/ከተሞች የህብረተሰቡ የልማት አገልግሎት እንዳይቋረጥ የልዩ ግዥ ፈቃድ ጥያቄ በማቅረባቸውና ፈቃድ በመስጠቱ ነው።

በግዥ ኦዲት የተገኙ ውጤቶች

- በ5 ዓመቱ ከህግ እና ከአሰራር ውጪ የሆኑ 6 ጨረታዎች እንዲሰረዙ ተደርጓል፣ ለአብነት፦ በ2014 ሳይንስራ ቴ/ል/ቢሮ፣ 2015- ትራፊል ማኔጅመንት ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በ 2016 የካቲት 12 ሪፈራል ሆስፒታል፤ በ 2017 የካ ክፍለ ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስ ፑል እና በ 2018 አራዳ ክፍለ ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስ ፑል ናቸው።
- በ5 ዓመቱ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት ውል እንዲቋረጥ እና ህጋዊ የግዥ መርህን ባልተከተለ መንገድ ሊፈጸም የነበረን 3 ግዥ ማስቀረት ተችሏል። ለአብነት፦ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ ፣ የካ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ ፣ ቂርቆስ ወረዳ 03 ፋይናንስ ጽ/ቤት ናቸው።
- በግዥ ኦዲት ተመላሽ የተደረገ የመንግስት ሀብት በ2014 እና በ2015 ብር የለም ፣ በ2016 ከባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ብር 842,000.00 ወደ መንግሥት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን የተደረገ፣ በ2017 ከክፍለ ከተሞች ብር 1,816,026.05 ወደ ፋይናንስ ቢሮ አካውንት ተመላሽ የተደረገ እና በ2018 ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን ብር 1,848,822.83 እና ከቂርቆስ ክ/ክ/ወረዳ 03 ፋይናንስ ጽ/ቤት ብር 84,000.00 በድምሩ ብር 1,932,822.83 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ስንት መቶ ሃያ ሁለት ከ83/100) ሲሆን፣ በ5 ዓመቱ ብር 4,590,848.88 ለመንግስት ተመላሽ ሆኗል።
- ከንግዱ ማህበረሰብ በግዥ አፈፃፀም ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን 100% ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሰረት፤ በ2014 በጀት ዓመት ለ37፣ በ2015 በጀት ዓመት ለ29፣ በ2016 በጀት ዓመት ለ60፣ በ2017 በጀት ዓመት ለ45 እና በ2018 በጀት ዓመት ለ47 በድምሩ በ5 ዓመቱ ለ218 ቅሬታዎች 100% ምላሽ ተሰጥቷል።
- ከባለበጀት መ/ቤቶች የአቅራቢዎች የጥፋተኝነት ሪፖርት 100 % ውሳኔ ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሰረት፤ በ2014 በጀት ዓመት 289፣ በ2015 በጀት ዓመት 318፣ በ2016 በጀት ዓመት 141፣ በ2017 በጀት ዓመት 267 እና በ2018 በጀት ዓመት 252 በድምሩ በ5 ዓመቱ 1267 የአቅራቢዎች የጥፋተኝነት ሪፖርት 100% ምላሽ ተሰጥቷል።

የኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ

- **በ2017 በጀት አመት በሙከራ ደረጃ በተመረጡ 13 ተቋማት ላይ የሲስተም ምዝገባ የተከናወነ ሲሆን አመታዊ የግዢ ፍላጎታቸዉን (Annual Procurement Plan) በሲስተም እንዲያሳወቁ ተደርጓል።**
- **በ2017 እና በ2018 በጀት ዓመት በተመረጡ 13 ተቋማት በአጠቃላይ 2917 ጨረታዎች የተከናወኑ ሲሆን በፐርቼዚንግ (Purchasing) 2,403 በግልፅ ጨረታ የወጡ 514 ጨረታዎች ተገምግመዉ ግዢ ተፈጽሟል። የተሰረዘ ምንም አይነት ጨረታ የለም ።**

ክፍል ሶስት

የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እና የቀጣይ የትኩረት

በጥንካሬ የታዩ

አብዛኛው በጀት ሰው ተኮር ተግባራት እና ዘላቂ ልማት መዋሉ

- **የመንግስት በጀት ለካፒታል ፕሮጀክቶች (ትምህርት፣ ጤና፣ ንጹህ መጠጥ ውሃ እና መሰረተ ልማት ወዘተ) እንዲዉል በማድረግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፣**
- **የሚመደበው በጀት የወደፊት የሀገርን የኢኮኖሚ አቅም የሚገነቡ እና የአካባቢ ጥበቃን ያገናዘቡ የረጅም ጊዜ ፕሮጀክቶች ላይ በማተኮሩ ለወደፊቱም ዘላቂ መሰረት የሚጥል መሆኑ።**
- **ውስን የሆነውን የህዝብ ሀብት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ላላቸው ስልታዊ መስኮች ላይ ማዋል መቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፤**
- **ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርአትን በመዘርጋት የመንግስትን ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግ ተችላል። ለአብነትም በኦዲት ግኝቶች ማስመለስ፣ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ወደተግባር እንዲገቡ መደረጉ፤**
- **ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሰራቱ የተቋሙ አፈፃፀም ከፍ እንዲል አድርጋል፤**
- **ፍትሀዊ እና አሳታፊ የበጀት ድልድል ስርአት መዘርጋት መቻሉ፤**

በውስንነት የታዩ

ሀ. አማራጭ ፋይናንስ ሞቢላይዝ ማድረግ አለመቻሉ

- ልማትን ለማፋጠን ከተለመደው የመንግስት ታክስና መደበኛ ገቢ ባሻገር ሌሎች የፋይናንስ ምንጮችን (ለምሳሌ፦ የመንግስትና የግል አጋርነት/PPP፣ የአረንጓዴ ፋይናንስ፣ ወይም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት) በበቂ ሁኔታ ስራ ላይ ማዋል አለመቻል።
- የአሰራር ስርአቱ ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ ምክንያት የመረጃ ልውውጥ መዘግየት፣ የተጠያቂነት እና የግልጽነት ጉድለቶች መስተዋሉ።

- ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃን በዲጂታል መንገድ በፈጠነ ሁኔታ ማግኘት አለመቻል፣ የክትትልና ግምገማ ስራዎችን እንዲሁም ስልታዊ ውሳኔዎችን በፍጥነት ለመስጠት እንቅፋት መሆኑ።
- የፕሮግራም በጀት አተገባበር ውስንነት መኖሩ፤
- በክትትል የተገኙ ግኝቶች ላይ የመንግስትን ሀብት ከማስመለስ አንፃር የተቋማት ውስንነት መኖሩ፤

ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች፦

- ነጻና ገለልተኛ የሆነ የውስጥ ኦዲት አለመደራጀት፣ የሰው ሀይል አለሚሟላት፣ ለስራ ምቹ ሁኔታ አለመኖር እና ለስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እንደ ኮምፒዩተሮች እና ሌሎች ግብአት አለመሟላት፣
- የሲስተም መቆራረጥ፤
- የተቋሙን ተልእኮ ለማሳካት የተሸከርካሪ ስምሪት በቂ ያለመሆን፤
- ህንፃው የኪራይ መሆኑ የተቋሙን አገልግሎት ምቹ እንዲሆን ለማድረግ የሚሰሩ ስራዎች ተግዳሮት እየገጠመ መሆኑ፤

የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ተደጋጋሚ ስልጠናዎችን በመስጠት ባመሉያዎችን የማብቃት ስራ በመስራት፤ የሰው ሀይል ለማሟላት፣ ለስራ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት መደረጉና ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ ተደርጓል፤
- ከኢትዮ ቴሌኮም እና ከሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር የሲስተም መቆራረጥ እንዲቀንስ ተደርጓል፤
- የተቋሙን ተልእኮ ለማሳካት የስራ ክፍሎች ተሽከርካሪን በቅንጅት እንዲጠቀሙ

በማድረግ ክፍተቱን ለመቀነስ ጥረት ተደርጋል፤

- ከህንፃው ባለቤት ጋር በመወያየት እና በማሳመን የተወሰኑ ችግሮች እንዲፈቱ ተደርጓል፤

የትኩረት አቅጣጫዎች

በወጪ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት ማጥበብ

- ያሉትን ውስን ሀብቶች ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች በቁጠባ ማዋል ።
- የታክስ አስተዳደርን በማዘመን፣ የታክስ መሠረቱን በማስፋት፣ የመንግስትን የገቢ አቅርቦት ማሳደግ።
- የወጪ ፍላጎት ከዕቅድ በላይ እንዳይሆን ጥብቅ የበጀት ቁጥጥር እና የፕሮጀክቶች ወጪ-ፋይዳ ትንተና (Cost-Benefit Analysis) ስርአትን ማጠናከር።

ተቋምን ሪፎርም እና ዲጂታላይዝ ማድረግ

- የተቋሙን መዋቅር፣ የተግባርና ኃላፊነት ክፍፍል እንዲሁም የስራ ሂደቶችን ውጤታማ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ተቋማዊ ማሻሻያዎችን መተግበር።
- የወረቀት ስራን የሚያስቀሩ፣ መረጃን በፍጥነትና በጥራት የሚያስተላልፉ እና የፋይናንስ አስተዳደር ስርአትን የሚያዘምኑ የተቀናጁ የሶፍትዌር ሲስተሞችን ስራ ላይ ማዋል፣
- የሪፎርም አስተሳሰብ እና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል ቀጣይነት ያለው የክህሎት ማሳደጊያ ስልጠናዎችን በመስጠት ብቁና ንቁ የሰው ሀይል ማፍራት፤
- የከተማውን እምቅ የገቢ አቅም የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን መከታተል፤ .

ማጠቃለያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ባለፈው አምስት የበጀት ዓመታት /2014-2018/ የተቋሙ የ10 ዓመት እና የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ ተመስርቶ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን በዉጤታማ በማድረግ የ5 ዓመቱን እቅድ አፈጻጸም በመገምገም ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ማድረግ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የ10 ዓመት እና የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ መሰረት ተደርጎ የአምስት ዓመቱን /2014-2018/ እቅድ አፈጻጸም የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን ውጤታማ በማድረግ የእቅድ አፈጻጸሙን በመገምገም እና ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ማድረግ ነው። እንዲሁም ባለፉት አምስት አመታት የተመዘገቡ ዋና ዋና ውጤቶች የሃብት አቅርቦት ማደጉ፣ ፍትሃዊ የሆነ የለዘላቂ ልማት በጀት ድልድል መካሄዱ፣ የበጀት አጠቃቀሙ እየተሻሻለ መምጣቱ፣ የመንግስት ፕሮጀክቶች የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ መሆኑ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና በመወጣት የዜጎችን የስራ እድል ተጠቃሚነት ማስፈን መቻላቸው፣ እና የፋይናንስ አሰራር ስርዓቱ እያደገና እየዘመነ መምጣቱ ዋና ዋና የተመዘገቡ ውጤቶች ናቸው።

ይሁን እንጂ ባለፉት አምስት ዓመታትእነዚህን ውጤቶች በማስመዝገብ ጎዞ የነበሩ ውስን ተግዳሮቶች ለመፍታት ሰፊ ጥረቶች ተደርገዋል። በዚህም ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለባለሙያዎች በመስጠት፣ የተሻሉ የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት መፍትሄ ተሰጥቷል።

በአጠቃላይ በርካታ ተግባራት በውጤታማነት የተከናወኑ መሆኑ በእያንዳንዱ ግብና አላማ ስር የተገለጸ ሲሆን በቀጣይ የአሰራር ስርዓትን ማዘመንና ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር ውጤታማነትን ለማረጋገጥ በትኩረት መስራትና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተግባራትን በቅንጅት እየገመገሙ መሄድ አስፈላጊ ይሆናል።

የፋይናንስ ቢሮ ከ2014 እስከ 2018 በጀት ዓመት /የ5 ዓመት/ እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ንፅፀር

	ስትራቴጅክ ግብ፣ ዋና ዋና ተግባራትና ዝርዝር ተግባራት/KPIs	መለኪያ	የ2014 በጀት ዓመት			2015 በጀት ዓመት			2016 በጀት ዓመት			2017 በጀት ዓመት			2018 በጀት ዓመት		
			እቅድ	ክንውን	በ%	እቅድ	ክንውን	በ%	እቅድ	ክንውን	በ%	እቅድ	ክንውን	በ%	እቅድ	ክንውን	በ%
ግብ-1	የሀብት አመዳደብ እና አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል፣																
ዓላማ-1	የልማት ሀብት አቅርቦት ማሳደግ፤	መቶኛ	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100
ዓላማ-2	ለዘላቂ ልማት የተመደበ የመንግስት በጀት በመቶኛ	መቶኛ	47.48	47.48	100%	50.68	56.5	111%	51.32	57.68	112	58	71.69	123%	72%	72%	100%
ዓላማ-3	በጀት አጠቃቀም በመቶኛ	መቶኛ	96.9%	97%	100%	97%	98%	101%	94%	99%	105%	99%	100	100	100	100	100
ዓላማ-4	የመንግስት ፕሮጀክቶች ፋይናንሻል አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ አፈፃፀም በመቶኛ	መቶኛ	98%	106%	106%	100%	104%	104%	100%	115%	115%	100%	103	103	100%	138	138%
ግብ-2	ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የተወጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ማሳደግ፣																

ዓላማ-5	ክትትልና ድጋፍ የተደረገባቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክቶች በመቶኛ	መቶኛ	78%	78%	100%	86%	84%	97%	89%	90%	100%	95%	100%	100%	85%	89%	105%
ዓላማ-6	ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በዘላቂ የገቢ ማስገኛ መስክ ተጠቃሚ ያደረጉ ድርጅቶች በመቶኛ፤	መቶኛ	12%	12%	100%	12%	13%	100%	13%	14%	100%	15%	19%	126%	15%	19%	126%
ግብ-3	የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፣																
ዓላማ-7	አመታዊ ሂሳባቸውን እስከ ነሐሴ 20 የዘጉ ተቋማት	መቶኛ	76%	76%	100%	79%	80%	100%	89%	89%	100%	94%	88.30%	94%	88%	77.10%	88%
ዓላማ-8	የቀነሰ ውዝፍ፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች በመቶኛ	መቶኛ	25%	15%	60%	28%	23%	82%	29%	24%	83%	35%	32.93	94%	38%	38%	100%
ዓላማ-9	የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የተገበሩ ተቋማት ሽፋን በመቶኛ	መቶኛ	25%	25%	100%	35%	35%	100%	45%	45%	100%	90%	90%	100%	100%	100%	100%
ዓላማ-10	IBEX ተጠቃሚ ተቋማት በመቶኛ	መቶኛ	80%	100%	100%	90%	90%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%

ዓላማ-11	ዘመናዊ የደሞዝ ክፍያ/ITAP/ ተጠቃሚ ተቋማት በመቶኛ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%	100%
ዓላማ-12	ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት ያቀረቡ መስሪያ ቤቶች በመቶኛ	መቶኛ	15	20%	64%/	75	77%	100%	81	81.6%	100%	82	82%	100%	82	85	100%
ዓላማ-13	ከሚፈጸሙ የመንግስት ግዢዎች የግልፅ ጨረታ ድርሻ በመቶኛ	መቶኛ	72%	77%	106%	83%	70%	84%	83%	70%	82%	83%	66%	80%	83%	67%	81%